<u>አረፈ ጥላዬ</u>

የምዕተ ዓመት ግማሽ ፣ ኪናዊ ቡራኬ፣ የትውልድ ውርርስ
የወገን መመኪያ፣ ያገር ሃብት ያገር ቅርስ፣
የሙዚቃው ንጉሥ፣ ቅላፄ አንደበቱ
የዜማው ርክርክ፣ ድፋቱ ቅናቱ፣
ተንግዲህ አበቃ፣ በአካል ተለዬ
ደከመ አሸለበው፣ አረፈ ጥላዬ።

እምቢልታ ይነፋ፣ ይጎሰም ከበሮ
መለያየት ሞት ነው፣ ይንጎርጎር ዘንድሮ፣
ማሲንቆ ክራሩ፣ ቫዮሊን ጊታሩ
ህልፈቱን ያውጁ፣ ዜናውን ይንገሩ።

ክላርኔት ትራምፔት፣ ሀዘን ይቀመጡ
መድረክ አጻራሾች፣ እርማቸውን ያውጡ፣
ድምቀት ፀጋቸውን፣ ብርቃቸውን ሲያጡ።

ባቲና አምባሰል፣ ትዝታ አንቺ ሆዬ፣ ጥቁር ማቅ ይልበሱ
እምባ እየተራጩ፣ አምርረው ያልቅሱ
ወትሮ የአንጀት ወዳጅ፣ ማ ለነሱ እንደሱ።

ጋሻ ጦሩ ይውጣ፣ ቀረርቶ ፉከራ ያጅቡት ጀግናውን
በድል ሲያጠናቅቅ ሲያበቃ ሩጫውን።

በፍጥረቱ ዕድገቷን
በሞቱ ድቀቷን፣
ጥበብ አፍ አውጥታ፣ ሀቁን ብትመሰክር
ደረቷን ብትጥል፣ ሙሾ ብትደረድር
በእውነት ማን ነበራት፣ ከሱ ወዲያ በምድር?

ቋንቋ አንደበት ሆንካት
በተክኖህ ምትሃት፣ ከብረህ አስከበርካት
ለእሷነቷ ሕልው፣ አድገህ አሳደካት፣

ፍቅርና ጥላቻን፣ ክፋት ደግነትን
የአገር አንድነት የጀግና ሰው ክብሩን
የሰብዓዊ ፍጡር መብት ነፃነቱን፣
በሰው ልጆች ሕይወት፣ በዉጣ ዉረዱ፣ያልጠቀስክ ያላልከው
ምን ርዕስ ይኖራል ፣ አንተ ያልጻሰስከው?

ስንኳን እኔ ቀርቶ፣ አብሬ ካንተ ጋር በዘመን የደመምኩ
የሕይወት ገመዴን በውልህ የቋጠርኩ፣
የሙዚቃን ቃና ካንደበት ልሳንህ፣ በስሜት የቆዘምኩ
በቅላፄህ ንግርት፣ ሀሴተ ጥበብን በእውን የታዘብኩ
እንዲያው በጥቅሉ፣ ለሙያ ብቃትህ መንፈሴን የገበርኩ፣

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የነገ ሕፃናት ገና ያልተወለዱት፣ ያዉቁታል እላለሁ የማይሞት ስራህን
ብቃት ችሎታህን፣ ረቂቅ ኃይልህን።

እንደነገስክበት፣ እንደኮራህበት
እሱ እንደተባልከዉ፣ ኖረህ አለፍክበት
ፀጋ በረከት ነዉ፣ በሕይወት መታደል
ታሪክህ ተነቦ፣ በስርዓተ ቀብር ግባ መሬት መባል።

ወደ ኋላ ትተዉ በሚያልፉት ልብ ያሉ
አሉ ይኖራሉ፣ ሞቱም አይባሉ፣

እናም፣
አንተን ሞተ ቢሉ ጥላሁን አረፈ
ሀቅ ነዉ አልክድም፣ የመድረኩ ግርማ በአካል አለፈ።
በመንፈስ ግን አለህ፣ ትኖራለህ ነገም
ጥለሁን ህያዉ ነህ፣ኗሪ ነህ ዘላለም።

አንተም ብለኸዋል ሞት ምርጫን አያዉቅም
ከእንክርዳድ ስንዴዉን ለይቶ አያቆይም፣
ሳይሆን ለማልቀሻ፣ ትንፋሽ ማስታወሻህ
ምስልና ስራህ ይቆማል ሐዉልትህ፣
የወገን አለኝታ፣ ታሪክ ነህ አሻራ
በአኩሪ ዜጋ ተግባር፣ ተጠቃሾች ጎራ።

በያንዳንዷ ዕለት፣ በሁላችን ምናብ
በኪናዊ ስራህ፣ባንተነትህ ድባብ፣
በዓይነ ህሊናችን እንደተብሰለሰልክ፣ በዜማ ቅላፄህ እንደተንቆረቆርህ
ሁሌ እንደታየኸን፣ ሁሌ እንደተደመጥህ፣ ሁሌ እንደተጠራህ
ዞትር ትኖራለህ ባካል ብትለይም
ጥላሁን አልሞትክም።

ከንጉሴ ጋማ
ለንደን

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com